16¾ ›mT qÜ_R 2
16th Year No 2

ÆHR ÄR ነሐሴ 12 ቀን 2003 ›/M
Bahir Dar August 18, 2011

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ZKr ÞG

# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

bx¥‰ B¼¤‰êE KL§êE mNG ሥT MKR b¤T «ÆqEnT ywÈ

**Issued Under the Auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ 1324
ÃNÇ ዋU BR 9.80
Unit price 9.80

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር 177/2003 ዓ.ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የስፖርት ኮሚሽንን ለማቋቋም**

**የወጣ አዋጅ**

**Content**

**Proclamation No. 177/2010**

**A Proclamation Issued to provide for the Establi- shment of Sport commission in the Amhara National Regional State**

## አዋጅ ቁጥር 177/2003 ዓ.ም

## በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የስፖርትና የአካል ማጐልመሻ እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት ይኸው የክልሉ ህዝብ ዓይነተኛ ባህል ሆኖ እንዲዳብር ማድረግ በማስፈለጉ፣

በክልሉ ውስጥም ሆን ከክልሉ ውጭ ከሚገኙ ከሌሎች ህዝቦች ጋር የተለያዩ ስፖርታዊ ውድድሮችን በማካሄድ ወንድማማችነትን ማጠናከርና የክልሉን አጠቃላይ ገፅታ ማስተዋወቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No. 177 /2010

## THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE SPORT COMMISSION ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHERE AS,** it has become necessary to promote sport and physical exercise activities in the Region and develop same as a core culture of the people there of;

**WHERE AS,** it is necessary to develop the bond of brother hood among peoples

reside with in and out side the region as well as to promote the general image of the region through conducting sport competition;



የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ''በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የስፖርት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 177/2003 ዓ/ም'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

1. ''ስፖርት'' ማለት ማንኛውም ግለሰብ እድሜና ፆታ ሣይገድበው ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ ለመዝናናት፣ አካሉን ለመገንባትና አይምሮውን ለማበልፀግ በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ በማናቸውም ጊዜና ቦታ የሚያከናውናቸውን የተለያዩ እንቅስቃሴዎችና የውድድር ስፖርቶች ያጠቃልላል።
2. ''የስፖርት ማህበር'' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ ውስጥ የተቋቋመ ስፖርት ነክ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ማህበር ወይም የስፖርት ፌዴሬሽን ነው።

NOW, THEREFORE, The Council of the Amhara National Regional State by virtue of the power vested in it under the provisions of Article 49 sub article 3(1) of the Revised Constitution of the National Region hereby issued this proclamation.

## PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as “the Amhara National Regional State Sport Commission Establishment Proclamation No.177/2010”.

**2. Definitions**

Unless the context requires other wise, in this proclamation:

1. `Sport` means that every one performs, with out age and sex limit, different activities including competition of sports, to take care of health, for recreation, physical strengthen and refreshing of mind in private or in group with and un organized manner at any time and place.

2. `Sport Association` means voluntary association of sport or a federation of sport established in the Region pursuant to this proclamation.



3. ''የስፖርት ክለብ '' ማለት በየደረጃው የሚቋቋሙ ፌዴሬሽኖችና ኮሚቴዎች ሥር የሚደራጁ ተጫዋቾችን፣ ስፖርተኞችንና ደጋፊዎችን የሚይዝ ማህበር ነው።

4. ''የስፖርት በጐ ፈቃድ ማህበር'' ማለት ስፖርተኞችና ተባባሪዎቻቸው በጋራ የተደራጁበት ሆኖ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውንም ሆነ ሀብታቸውን በማስተባበር ለካባቢያቸው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጥ ማህበር ነው።

5. ''የስፖርት ፌዴሬሽን'' ወይም ''ኮሚቴ'' ማለት በክልሉ ውስጥ አንድን የስፖርት እንቅስቃሴ ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተጣለበት ህዝባዊ አደረጃጀት ነው።

6. ''የስፖርት ምክር ቤት'' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በክልሉ ውስጥ ከተለያዩ መንግሥታዊ፣ ህዝባዊ ድርጅቶችና የስፖርት ፌዴሬሽኖች ወይም ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ የተቋቋመ የአማራ ብሔራዊ ክልል የስፖርት ምክር ቤት ነው።

3. `Sport Club` means an association embracing players, sportsmen and their supporters hierrarchically established under Federations and Committees.

4. `Voluntary Association of Sport` means an association wherein sportsmen and their collaborators are organized together by coordinating their time, labor, knowledge and property and thereby render services to their surrounding societies;

5. `Federation of Sport` or `committee` means public organization responsible for the management and expansion of one type of sport activity in the Region.

6. `Council of Sport` means the

council of sport of the Amhara National Region, established under this proclamation constituting of different governmental and public organizations as well as Federations of Sport or Committees.



## ክፍል ሁለት

### ስለ ኮሚሽኑ መቋቋምና አላማ

### 3. ስለመቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስፖርት ኮሚሽን / ከዚህ በኋላ ''ኮሚሽኑ'' እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

### 4. አላማዎች

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፦

1. ስፖርት በክልሉ ህብረተሰብ ዘንድ እንዲሰርጽ እና ህዝባዊ ባህል እንዲሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ፤
2. በክልሉና ከክልሉ ውጭ በሚደረጉ ስፖርታዊ ውድድሮች በህዝቦች መካከል ወንድማማችነት እንዲዳብር ማድረግ፣
3. የክልሉን ብቁ ስፖርተኞች ማፍራትና የስፖርት ኢንቨስትመንት የሚስፋፋበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር።

# PART TWO

## Establishment and Objectives of the Commission

### 3. Establishment

1. The Sport Commission of the Amhara National Regional State / here inafter referred to as the `Commission'/ hereby established an autonomus organ of the Region governmenthaving its own legal personalities, as per this proclamation.
2. The commission shall be accountable to the Head of Government of the Region.

### 4. Objectives

The commission, pursuant to this proclamation, shall have the following objectives:

1. To make the necessary effort to inculcate sport in the society and there by help same become the culture of the people of the Region;

2. To develop the bond of brother hood among people through inter, and intra-Regional Sport Competitions;

3. To produce competent sportsmen and women as well as create conducive condition for the expansion of sport investement.



## 5. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በዞኖች፣ በከተማም ሆነ በወረዳ አስተዳደሮችና ሌሎች የበታች ያስተዳደር አርከኖች የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ይኖሩታል።

## ክፍል ሦስት

## የኮሚሽኑ ልጣንና ድርጅታዊ አቋም

## 6. የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር

ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና

## 5. Head Office

The head Office of the Commission shall be in Bahir Dar; and may have branch Offices to be established at Zones, City and Woreda administrations, and other hierarchically lower administrative levels, as may be necessary.

# PART THREE

## Powers and Organizational Structure of the Commission

ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ስፖርትን በተመለከተ የወጡ አገር አቀፍ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በአግባቡ ሠርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲተገበሩ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. የክልሉን ስፖርት እድገት እውን የሚያደርጉ ህጐችንና ደንቦችን በማውጣት ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ ያስፀድቃል፣ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

## 6. Powers and Duties of the Commission

Pursuant to this proclamation, the Commission shall have the following powers and duties:

1. Work for ,follow up, coordinate and oversee the proper internalization and execution of those policies and strategies Nationally issued regarding to sports, throughout the Region,
2. Initiate laws and regulations, necessary to realize the development of Sport of the region, and thereby present to the concening bodies to be promulgated; follow up and oversee the execution of same;



3. በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ስፖርቶች ሊስፋፉባቸው የሚችሉባቸውን አካባቢዎች ወይም ለስፖርቱ እድገት የሚውሉትን የተፈጥሮ ጸጋዎች በመለየት በልዩ ሁኔታ የስፖርት ፕሮጀክቶችንና ተቋማትን ያቋቁማል፤ ተገቢውን ድጋፍና ክትትልም ያደርጋል፤
4. በክልሉ ውስጥ ለሚገነቡት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የስልጠና ማዕከላት ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በየደረጃው እንዲገነቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣ የሕግ ከለላ እንዲኖራቸው ድጋፍ ይሰጣል፣
5. የክልሉን ስፖርት ነክ መሠታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ያሠራጫል፣ ለስፖርቱ

3. Establish, in a special circumstance, projects and institutions of sport; by identifying areas where different sports to be expanded or the natural potentials applied to the development of same in the Region; and provide the proper support and follow up thereof;
4. Prepare standards for gymnasiums and training centers

ልማት ዘርፍ የሚጠቅሙ የጥናትና የምርምር ሥራዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣

6. በስፖርቱ የልማት ዘርፍ የተሰማራውን ሙያተኛ አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ የረጅምና የአጫጫር ጊዜ ስልጠናዎችን ያመቻቻል፤
7. የስፖርት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሠጭ ወጣቶቸን በስፋት በማደራጀትና በማቋቋም ለዘርፉ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ ያደርጋል፤
8. የሕብረተሰብ አቀፍ ስፖርት ተሣትፎ ፕሮግራም ወይም ፓኬጅ፣ በማዘጋጀት ማህበረሰቡ በሚኖርበት፣ በሚሠራበትም ሆነ በሚማርበት አካባቢ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተሣታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፣

throughout the Region, cause such facilities to be constructed and render service at various levels, and give support to get legal protections,

5. Collect and organize basic information in relation to sport in the Region, and tansmit same to the relevant bodies; and cause study and research activities, important for the sport development sector, to be conducted thereon;

6. Facilitate long and short term training to strengthen the capcity of professionals working in sport development sector;

7. Organize and establish widely youths rendering voluntary sport services and thereby cause them to highly contribute to the sector;
8. Having prepared the mass sport participation programs or packages, cause the people participate in and henceforth benefit from sport activities in their habitat, working and learning environment;



9. የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም የስፖርት ገቢዎችን ያሰባስባል፣ ለታለመላቸው ዓላማ ያውላል፣ የስፖርት ማህበራት የሚሰበስቡት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈጸሚያ ብቻ

9. Collect, using various revenue-raising mechanisms, sport incomes and employ same for the

መዋሉን ለማረጋገጥ ሂሳባቸውን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፤

10. በክልሉ ውስጥ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሃብቶች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ በስታንዳርዱ መሠረት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

11. አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በወጣት ማእከላት፤ በታላላቅ ሆቴሎች፣ ሪል-ስቴቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶችና በመሳሠሉት ሌሎች አካባቢዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥሪያ ቦታዎች ተካተው መሠራታቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ይሰጣል፣

12. ስፖርት ለስራ ፈጠራ የሚኖረውን ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት በሽያጭና በዝውውር አማካኝነት በክለቦች የሚታቀፉ ስፖርተኞች የጉልበት ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ድጋፍ ያደርጋል፤ የስልጠና ማዕከል ከፍተው የራሳቸውን ስራ ለሚፈጥሩ አካላት ሁሉ ተገቢውን ድጋፍና ክትትልም ያደርጋል፤

13. በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ለሚቋቋሙ የስፖርት ማህበራት ስታንዳርድ ያወጣል፣ በስታንዳርዱ መሠረት ያቋቁማል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሥራ ውል ይይዛል፣ ፕሮግራማቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

intended purpose as well as audit and supervise the accounts of the sports' association in an effort to ascertain that the revenue they may have collected is utilized only for the accomplishment of their purposes;

10. Prepare standards for investors wishing to engage themselves in sport investment in the Region ; issue and supervise professional license in line with such standards thereof;

11. Follow up and render support to, in consultation with the concerned bodies, the accommodative use of physical exercise undertaking sites within the premise of youth centers, grand hotels, Realstates, hospitals, schools and other similar institutions;

12. Provide support, considering the importance of sport to invention of work, to sportsmen and women embraced in clubs to be protected from labour exploitation due to sales and transfer; support and followup bodies who open their own work through opening training center;

13. Issue standards to the establishment of sport associations at various levels in the Region ; cause same to be established as per such standards; issue license, enter

into working contracts; coordinate and supervise the programs of same thereof;



14. በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የስፖርት ም/ቤቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

15. በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር በስፖርታዊ ችግሮች ዙሪያ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በጥናቱ ውጤት መሠረት ተፈፃሚ ያደርጋል ፣

16. ክልላዊ የስልጠና ስታንዳርዶችንና የአቅም ግንባታ ፓኬጆችን በማዘጋጀት ከክልሉ ትምህርት ቢሮ እና ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር፣ ለስፖርት አመራሮችና ባለሙያዎች፣ ለአሰልጣኞችና፣ ለስፖርተኞች ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

17. የክልሉን ስፖርታዊ ውድድሮች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ውድድሮችን ያካሂዳል፣ ውድድር እንያዲዘጋጁም ተገቢውን ፈቃድ ይሰጣል፤

18. ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማህበራትና በሌሎች አካላት መካከል የሚነሱ ክርክሮችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሳጣል፣

19. በክልሉ ውስጥ ባህላዊ ስፖርቶች የበለጠ እንዲታወቁና የራሣቸው ሕግና ደንብ የሌላቸውም ይኸው እንዲወጣላቸው ይሠራል፣ እንዲሻሻሉና እንዲያድጉ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

14. Cause the establishment and strengthening of the sports' councils at various levels in the Region;

15. Carry out studies in relation to problems of sport in collaboration with higher educational institutions found in the Region; and thereby implement as per the out come of the same;

16. Cause the provision of trainings, in collaboration with Education Bureau of the Region and Higher Educational Institutions, for leaders and professionals of sport, for coaches and sportsmen and women up on the preparation of Regional training standards and capacity building packages ; follow up the implementation of same thereof;

17. Prepare standard for the Regional Sport competitions; undertake sport competitions in collaboration with relevant bodies; and issue license for those wishing to undertake same;

18. Adjudicate desputes that

may arise among sport associations and other bodies in relation to Regional sport competitions and thereby render administrative decisions;

19. Work for the popularization of traditional sports and the issuance of laws and regulations devoid of same in the region ; encourage and provide support to the improvement and growth there of ;



20. ከሕብረተሰቡ አቅም ጋር የተገናዘቡ የስፖርት ትጥቆችና መሣሪያዎች በክልላችን የሚመረቱበትንና ከሐገር ውስጥም ሆነ ከውጪ በድጋፍ መልክ የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

21. ስፖርትን በማስፋፋትና በማነልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ የስፖርት ማህበረሰቦች፤ ግለሰቦች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግልፅ መመሪያ በማዘጋጀት የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሠጣል፣ ለበለጠ ሥራ ያነሳሳል ፤

22. ከክልሉ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲና ሌሎች የሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎችና የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶች በሬዲዬም ሆነ በቴሌቭዥን እንዲተላለፉ በቅርብ ይሰራል፤

23. ከክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመተባበር ከስፖርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጤና ነክ ጉዳዮች በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ያደርጋል።

## 7. <u>የሥራ አመራርና ድርጅታዊ አቋም</u>

**ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት ለማከናወን የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦**

20. Facilitate conditions where by sport equipment and instruments be produced in the Region; and their availability from domestic and external sources in the form of support;

21. Hand over awards to, up on the preparation of clear directives, sport societies, individuals, civic associations, governmental and non governmental organizations for their high contribution to the promotion and development of sport; and thereby motivate for additional work;

22. Work closely, in collaboration with the Mass Media

1. ክልል አቀፍ የስፖርት ምክር ቤት፤

Agency of the Region and other media organizations, for the transmition of important physical exercises and awareness creating educations through radio and on television;

23. Implement health issues related to sport with a prior plan in collaboration with Bureau of Health of the Region;

## 7. Management and Organizational Structure

The commission shall have the following bodies to implement the powers and duties given under Article 6 of this proclamation:

1. The Regional Sport Council ;



2. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾሙ ኮሚሽነርና ም/ኮሚሽነር፤

3. አንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች።

## ክፍል አራት

## ስለ ኮሚሽነሩ

## 8. የኮሚሽነሩ ስልጣንና ተግባር

2. Commissioner and Vice commissioner appointed by the Head of Regional Government;
3. Other subordinate heads and employees as may be necessary.

# PART FOUR

## Commissioner

## 8. Powers and Duties of the Commissioner

ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለኮሚሽኑ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት የማስፈፀም ኃላፊነት ሲኖረው በተጨማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. የኮሚሽኑን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የኮሚሽኑን እቅድና በጀት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
3. የጥናትና ምርምር ተግባራት እንዲከናወኑ፣ የስታስቲክስ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና እንዲቀነባበሩ በማድረግ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና እንደሁኔታው ለፌዴራሉ መንግሥት የስፖርት ኮሚሽን ያስተላልፋል።

The commissioner being accountable to the Head of Regional government and responsible to implement the powers and duties given under Article 6 of this proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Direct and administer the activities of the commission;
2. Cause the preparation of plan and budget of the commission; and upon approval, implement same;
3. Cause the undertaking of studies and research; collection and compilation of statistical data; and transfer same to the Council of the Regional Government, and as the case may be, to the Sport Commission of the Federal Government;



4. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፣
5. ለኮሚሽኑ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣
6. ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በየጊዜው የሥራ ዘገባዎችን ያቀርባል፣
7. ለሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን ለበታች የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል።

4. Represent the commission in its dealings with third parties;
5. Efffect financial expenditure according to the budget and action plan of the commission; and supervise the implementation of same;
6. Submit, regarding its activities performance report to the

## 9. ስለ ምክትል ኮሚሽነሩ

1. ምክትል ኮሚሽነሩ በኮሚሽነሩ አቅራቢነት በርዕሰ መስተዳድሩ ይሿማል።

2. የምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነት ለኮሚሽነሩ ይሆናል።
3. ምክትል ኮሚሽነሩ ፦

   ሀ/ በኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

   ለ/ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

council of the Regional Government.

7. Transfer, where it found necessary for the efficiency of the work, his powers and duties by delegation to his subordinates.

## 9. Deputy Commissioner

1. The deputy commissioner shall be appointed by the Head of Government upon recommendation by commissioner.
2. The deputy commissioner shall be accountable to the commissioner.
3. The deputy commissioner:
   a. implement the duties given by the commissioner,

   b. Act on behalf of the commissioner in the absence or under circumstance when he is unable to perform his normal duties.



## ክፍል አምስት

## ስለ ክልሉ ስፖርት ምክር ቤት መቋቋምና

# PART FIVE

## የአባላት ጥንቅር

### 10. ስለ ምክር ቤቱ መቋቋምና የአባላት ተዋፅኦ

የአማራ ክልል ስፖርት ምክር ቤት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ሲሆን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

1. በርዕሰ መስተድድሩ የሚሰየም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተወካይ .....ሰብሣቢ፤
2. የየዞኑ ስፖርት ምክር ቤቶች ሰብሳቢዎች .....አባላት፤
3. የየዞኑ የስፖርት ምክር ቤቶች ሥራ አስኪያጆች.....አባላት፤
4. የኢያንዳንዱ ክልል አቀፍ ስፖርት ፌዴሬሽን ወይም ኮሚቴ ሊቀመንበር .....አባል፤
5. ታዋቂ የስፖርት ደጋፊ ግለሰቦች .....አባላት፤
6. በክልሉ መንግሥት የሚሰየሙ አግባብ ያለቸው መንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮች .....አባላት፤
7. የስፖርት ኮሚሽነሩ.....ፀሐፊ።

## Establishment and Composition of Members of the Regional Sport Council

### 10. Establishment and Composition of Members in the Council

The sport council of the Amhara Region shall be established under this proclamation and have the following members:

1. Representative of the council of Regional Government nominated by the Head of Government of the Region……chairperson;
2. Chairpersons of Zonal Council of sports ……members;
3. Managers of zonal sport councils…… members;
4. Chairperson of each Regional sport Federation or Committee……. Member;
5. Known private supporters of sport ……members;
6. Appropriate representatives of governmental and public organizations to be assigned by the Regional State ….. members;
7. Commissioner of the Sport Commission ……. Secretary.

## 11. የምክር ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ስፖርት ስለሚስፋፋበትና ስለሚዳብርበት ሁኔታ ተወያይቶ የውሣኔ ሀሣብ ያቀርባል፣
2. የፖሊሲ ውሣኔዎችንና የረዥም ጊዜ እቅዶችን በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈድቅም በሥራ ላይ ያውላል፤
3. ኮሚሽኑ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች መርምሮ ያፀድቃል፤
4. ለስፖርቱ አገልግሎት የሚያስፈልገው ወጭ ተዘጋጅቶ ሲቀርብለት ይህንኑ መርምሮ ያፀድቃል፤
5. የኮሚሽኑን የሥራ እቅድና ሪፖርት ይገመግማል።

## 12. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

1. ምክር ቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል፣
2. ከምክር ቤቱ አባላት አብዛኛዎቹ በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምለዕተ ጉባዔ ይሆናል፣

—

## 11. Powers and Duties of the Council

—

The council, under this proclamation, shall have the following powers and duties:

1. Submit, through discussion, its recommendations as to the expansion and development of sports at all levels in the Region;
2. Prepare and submit policy recommendations and long -term plans to the Regional State; and implement same upon approval ;
3. Examine and approve directives issued by the commission;
4. Examine and approve the necessary expenditure for sport service;
5. Evaluate the work plan and performance report of the commission.

## 12. Meeting and Decision making Procedure of the Council

1. The regular meeting of the

council shall convene once in a year; however, extraordinary meetings shall be held at any time, as may be necessary;

2. The presence of majority members of the council shall constitute a quorum;



3. የምክር ቤቱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባና የውሣኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

3. Decisions of the council shall be passed by simple majority vote; however, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
4. Without prejudice to the provisions of this Article, the council shall adopt its own meeting and decision making procedural rules.

## 13. ስለ ዞንና የወረዳ ስፖርት ምክር ቤቶች አወቃቀርና ተግባር

## 13. Structure and Duties of the Zone and Woreda Sport Council

1. በክልሉ ውስጥ ባሉት ዞኖችና ወረዳዎች የስፖርት ምክር ቤቶች ይቋቋማሉ።
2. የበታች ስፖርት ምክር ቤቶች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በኮሚሽኑ በሚዘጋጅና የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወሰን ይሆናል።

1. The councils of sport shall be established at zones and woredas in the Region. _
2. The detailed duties and responsibilities of the subordinate sport councils shall be determined by a regulation, prepared by the commission following this

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14. ስለ በጀት

የኮሚሽኑ በጀት በክልሉ መንግሥት ይመደባል።

## 15. ስለ ሂሣብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል፣
2. የኮሚሽኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ

ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ።

proclamation and issued by the Council of the Regional Government.

# PART SIX

## Miscellaneous Provisions

### 14. Budget

The Regional State shall allocate budget of the commission.

### 15. Book of Accounts

1. The commission shall keep accurate and complete financial accounts.
2. The book of accounts and documents of financial and property of the commission shall be frequently audited by the Office of the Auditor General of the region or auditors delegated thereon.



### 16. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 17. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

ስፖርትን በሚመለከቱ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 167/2001 ዓ/ም ተቋቁሞ ለነበረው የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው ኮሚሽን ተላልፈዋል።

### 18. ደንብ የማውጣት ስልጣን

### 16. Inapplicable Laws

Any proclamation, regulation, directives or practice contrary to this proclamation, shall be inapplicable on matters provided in this proclamation.

### 17. Transfer of Rights and Obligations

Rights and obligations pertinent to

ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል።

## 19. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ነሐሴ 12 ቀን/2003 ዓ/ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚደንት

sports vested in the Bureau of Youths and Sports Affairs of the Region established under proclamation No. 167/2009 are hereby transferred to the commission established by this proclamation.

## 18. Powers to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation there of.

## 19. Effective Date

This proclamation shall come in to force as of its publication date in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 18th day of August, 2011.
Ayalew Gobezie
President of the Amhara National Regional State